የወ/መ/ቁጥር 148028

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ ዋና ሳጅን ቢያ አባገላን አባሮሮ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም በተሻፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሰው ላይ ፍርሀትንና ድንጋጤን በሚቀሰቅስ ሁኔታ ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 1፡30 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ደስታ ኩሪን በጥይት እገልሻለሁ፤ አጠፋሻለሁ በማለት በቀጥታ በመናገር ያስፈራራትና የዛተባት በመሆኑ በፈፀመው የዛቻ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮቹን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ ተከሳሽ የግል ተበዳይን እገልሻለሁ በማለት የዛተ መሆኑን በማስረዳታቸው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ስር እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዟል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብሎ ሦስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የሚሰሙበት ጭብጥም በዕለቱ በጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም ምሽት 2፡00 ሰዓት ከት/ቤት ወጥቼ ወደ ቤቴ ልደርስ ስል ወ/ሮ ደስታ እና የእኔ ባለቤት ይጨቃጨቁ ነበር፤ ይህም የሆነው በራችን ፊት ለፊት ነበር፤ ከዚያም ባለቤቴን ወደ ቤት አስገብቼ በሬን የዘጋሁ ሲሆን፤ ወ/ሮ ደስታ ግን በሩን ገፍትራ ወደ ቤቴ ውስጥ ገባችኝ፤ እኔም በዚህ ጊዜ በሕግ አምላክ እኔ ደክሞኛል፤ እረፍት እፈልጋለሁ ቤቴ ውጭልኝ ማለቴን እንጅ ሌላ ነገር አለመፈፀሜን አስረዳለሁ የሚለውን ሲሆን በዚሁ መሰረት የመከላከያ ምስክሮች እንደ እምነታቸው መኃላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ አስተብብሏል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች እንደ ተከሳሽ ጭብጥ አቀራረብ ያስረዱ ቢሆንም በግል ተበዳይና በተከሳሽ መካከል በወቅቱ ጭቅጭቅ የነበረ መሆኑን የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮችም የገለፁት ጉዳይ በመሆኑ፤ እንዲሁም የተከሳሽም ሆነ የግል ተበዳይ ጓደኝነትም ሆነ ዝምድና የሌላት ነገር ግን የሁለቱም ግለሰቦች

ጎረቤት የሆኑት የፀ/ሕግ ሁለተኛ ምስክር እንዳስረዱት በወቅቱ የግል ተበዳይ እና የተከሳሽ ባለቤት ይጨቃጨቁ እንደነበርና በዚህ ጊዜም ተከሳሽ መጥቶ በክሱ ላይ የተገለፀውን የዛቻ ድርጊት የፈፀመ መሆኑን በግልፅ ያስረዱ ስለሆነ፤ ተከሳሽ ድርጊቱን አልፈፅምኩም በማለት አቀርቦ ያሰማቸውን ምስክሮች ቃል ፍ/ቤቱ እምነት የሚጣልበት ሆኖ ያላገኘው ስለሆነ ተከሳሽን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ፀ/ሕግ</u>፡ ፍ/ቤቱ የወንጀል ደረጃውን ሲያወጣ ተከሳሽ የፖሊስ አባል ሆኖ እያለ
ይህን ድርጊት መፈፀሙ እና በመሳሪያም እገልሻለሁ ስላለ ከባድ ተብሎ
እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 39 ዓመት ነው፤ ሥራዬ የፖሊስ አባል ሲሆን የምስራውም
በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦርሚያ ልዩ ዞን ውስጥ ነው፤ ትዳር አለኝ፤ አንድ
የ 11 ዓመት ልጅ አለኝ፤ ባለቤቴ ሥራ የላትም፤ የወር ገቢዬ ብር
960.00(ዘጠኝ መቶ ስልሳ ብርፊ) ነው በማለት አመለከተ።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580/የዛቻ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደኛ ተከሳሽ ወንጀሉን የፈፀመው ገዳይ መሳሪያ የሆነውን የጦር መሳሪያ ይዞ በመሆኑ የደረጃውን ሁኔታ ከፍ የሚያደርገው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን ሰዎች ባሉበት የተፈፀመ ስለሆነ፤ የወንጀል ደረጃው መካከለኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 580 ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአስር ቀን እስከ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ቀላል እስራት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት መካከለኛ ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከሃምሳ ሁለት ቀን እስከ ዘጠና አምስት ቀን ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት ሰባ አምስት ቀን መነሻ ቅጣት ተብሎ ተወስኗል።

ይህ በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ እርከን 2 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቃደ ስልጣኑም/range/ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት ሁለት ወር እስራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84 እና 85 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስላላቀረበ ከላይ የተመለከተው እርከን ከፍ አልተደረገም።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 ላይ በተገለፀት መሰረት አላቀረበም። ስለሆነም ፍ/ቤቱ ከላይ የተመለከተውን የቅጣት እርከን ዝቅ አላደረገውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 2 ላይ በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ባለመኖሩ በሁለት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ በአሁኑ ወቅት አንድ የ 11 ዓመት ልጅ ያለው ሲሆን፤ ባለቤቱ ሥራ
ስለሌላት የቤተሰቡ አስተዳዳሪና የገቢ ምንጭ ተከሳሽ መሆኑን ከግንዛቤ
በማስገባት ለተከሳሽ አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የወደፊት አመልና
ፀባዩን ማየቱ በቂ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ስለገመተ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል
ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሁለት ዓመት ገደብ አግዶታል።

2 ኛ. ተከሳሽ ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆን ዘንድ ለብር
500.00(አምስት መቶ ብር) የሚበቃ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197(2) መሰረት

ይጥራ። ሲጠራና ለፅህፈት ወጪ ብር 25.00(ሃያ አምስት ብር) ሲከፍል ተከሳሽ ይለቀቅ። ይፃፍ።

3 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

4 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

5 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።